# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 150 መጋቢት 22 2003 ገጽ 1


**አገራችን ሃብታም፤ ህዝቧም ታታሪ መሆኑን እናውቃለን። በድህነት ላይ የቆረጠ መንግሥት ሳይኖረን ድህነትን ማስደንገጥ እንኳን አንችልም። ከድህነት የመውጫ መንገድ የሚጀመረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ማስወገድ መሆኑ ዛሬ የማያሻማ ሃቅ ሆኗል።**

**ድህነት በቃን!!! የድህነት ሽሪክ የሆነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቃን!!! ድህነትና መለስ ይወገዱ!!!!!**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በመለስ ዜናዊ የሚታዘዙ ፖሊሶች ለተቃውሞ ሰልፍ በወጡ ኢትዮጵያዊያን ላይ ጉዳት አደረሱ

ዘረኛውና አምባገነኑ የትግራይ ገዢ ጉጇሌ ፖሊሶች መጋቢት 20 በአዲስ አበባ ከተማ ባለው የእስራኤል ኤምባሲ ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ወደሥፍራው በመንቀሳቀስ ላይ በነበሩ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የተለመደውን ሰብአዊነት የጎደለው የጥቃት እርምጃ በመውሰድ በርካታ ሰዎችን እንደደበደቡና በጽኑ እንዳቆሰሉ ከሰማኒያ በላይ የሚሆኑትን ደግሞ ወደ እስር ቤት ወሰደው እንዳጎሩ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓም ከእስራኤል ኤምባሲ ፊት ለፊት ባለው ቦታ ሊካሄድ በታሰበው የሰላማዊ ሰልፍ ለመሳተፍ ቁጥራቸው ወደ ሁለት ሺህ የሚገመት ሰው የመንገድ ላይ እንቅስቃሴ ጀምሮ እንደነበር የታወቀ ሲሆን ይህንን ሰላማዊ ሰልፍ ተከትሎ በርካታ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ በመቀላቀል የአገዛዙን እድሜ አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል ከሚል ስጋት እንደሆነ ለግዳጅ ከተሰማሩ ፖሊሶች ለማወቅ ተችሎአል። ሰላማዊ ሰልፉን ያደራጁ የቤተእስራኤል ዝርያ እንዳላቸው የሚናገሩ ዜጎች ሲሆኑ ጥያቄያቸውም የነበረው የእስራኤል መንግስት የዜግነት መብታቸውን እንዲጠብቅና እንዲያረጋግጥ ጥያቄ ለማቅረብ ነበር። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## አባዱላ ገመዳ ወያኔን ጥሎ ለመኮብለል ሃሳብ እንዳለው ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ

የኦሮሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት በምህፃረ ቃሉ ኦህዴድ በመባል የሚታወቀውን የህወሃት ተለጣፊ ድርጅት ከመሰረቱት እና ለረጂም ጊዜ ከፍተኛ አመራር ሲሰጡ ከኖሩት አንዱ የሆነው አባዱላ ገመዳ በህወሃት ሲደርስበት የኖረው የአካልና የስነልቦና ጫና አንገሽግሾት አገር ጥሎ ለመኮብለል ሃሳብ እንዳለው ለግለሰቡ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በስልክ አስታወቁ።

አንደምንጮቻችን መረጃ አባዱላ ገመዳ በህክምና ሰበብ ከአገር ወጥቶ ላለፉት 2 ሳምንታት በጀርመን አገር ለደህንነቱ ሲባል ስሙን ለመግለጽ ባልተፈለገበት ከተማ ውስጥ ይገኛል። ህወሃት ለሁለት በተከፈለበት ወቅት ከነአቶ ስዬ ቡድን ወግነሃል ተብሎ ከኦህዲድ ሰብሳቢነቱና ከኦሮሚያ ፕረዝደንትነቱ ተባሮ በነበረው ኩማ ደመቅሳ ምትክ ተተክቶ ኦሮሚያንና ኦህዲድን ሲመራ የነበረው አባዱላ ገመዳ፤ ህወሃት በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የዘረጋውን የትግራይ የበላይነት ሽፋን ሊሰጥ ይችላል በሚል ታሳቢ የመከላኪያ ሚንስቴርነት ሹመት ተሰጥቶት እንደነበረ፤ በዚያ ሹመት ላይ በቆየባቸው ጊዜያቶች በሥልጣን የበታቾቹ በነበሩ የትግራይ ተወላጅ የህወሃት አባላት ምንም አይነት የረባ ሥልጣን እንዳልነበረው እንዲያውቅ ሲደረግ እንደነበረ ሲያማር ኖሮአል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንፈሱና ባህሪው ተለውጦ ከመለስ ዜናዊ ጋር የነበረው መግባባት ሁሉ እያሽቆለቆለ እንደመጣና ከፍተኛ ወደ ሆነ አለመግባባት እንደተቀየረ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ። **ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## የኦሮሞ ነጻነት ግምባር ወታደሮች 22 የወያኔ ወታደሮችን መግደላቸውን አስታወቁ

በምህጻረ ቃሉ ኦነግ በመባል የሚታወቀው የኦሮሞ ነጻነት ግምባር ወታደራዊ ሃይል በምስራቅ ሃረርጌ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኝ የወያኔ አገዛዝ ወታደራዊ ሃይል ላይ በወሰደው ርምጃ 22 የዘረኛው አገዛዝ ወታደሮችን መግደሉን እንዲሁም ሌሎች ሃያ አምስት እታደሮች ደግሞ በማቁሰል ከጥቅም ውጭ ማድረጉን ገልጹአል።

በዚሁ ክልል በተካሄደው ወታደራዊ ውጊያ የኦሮሞ ነጻነት ግምባር ሃይል በርካታ ወታደራዊ ቁሳቁሶችንና የጦር መሳሪያ የማረከ መሆኑን ተያይዞ የወጣው ዜና አመልክቱአል።

የኦነግ ወታደራዊ ሃይል እንደፈረንጆች አቆጣጠር ከማርች 12 ቀን ጀምሮ ጋራ ሙለታና ማዩ ሙሉቄ በተባለና ጋራ ዋሎ በሚባለው ቦታ ላይ ይገኝ የነበረውን የዘረኛውን አገዛዝ ወታደራዊ ሃይል በቅርበት ሲከታተል ከቆየ በሁኣላ ስድስት ወታደሮችን መግደሉን እንዲሁም ሌሎች 18 ወታደሮችን ማቁሰሉን እንዲሁም እንደፈርንጆች አቆጣጠር ማርች 17 ቀን በምስራቅ ሃራርጌ ባቢሌ ተብሎ በሚታወቅ ወታደራዊ ካምፕ ላይ በሰፈሩት ወታድሮች ላይ ጥቃት ፈጽሞ 14 ወታደሮችን መግደሉን እንዲሁም ሌሎች ሰባት ወታደሮችን **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ወጣቶችን ለውትድርና ማፈስ መጀመሩ ታወቀ

መውደቂያ ጊዜው መቃረቡ የታወቀው ዘረኛውና አምባገነኑ የትግራይ ገዢ ጉጇሌ ቡድን ወጣቶችን በማስገደድ ውትድርና ውስጥ እንዲገቡ በሌሊት ከየቤታቸው እያፈሳቸው መሆኑን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ ገለጸ። በትክክል እየሆነ ያለው ወጣቶችን በሌሊት ከየቤታቸው በማፈስ ወደ ካምፕ ማሰባሰብ መሆኑ በአደባባይ እየታየ፣ ዘረኛው የትግራይ ገዢ ጉጇሌ በቁጥጥሩ ስር ባዋላቸው ሚዲያዎች አማካኝነት ከስምንተኛ ክፍል በላይ የሆኑ ወጣቶች ለውትድርና እንዲመዘገቡ ጥሪ በማድረጋ ላይ መሆኑን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል።

ቀደም ብሎ የነበረው የደርግ አገዛዝ መውደቂያው ሲቃረብ እጂግ በርካታ ወጣቶችን ወደ ውትድርና ዓለም በግዴታ እየመለመለ ሲያስገባ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ደርግ በጦር ሃይል ብዛት ስልጣን ላይ ተፈናጦ መቆየት አለመቻሉን ባይኑ ያየው ይህ ዘረኛና አምባገነን ስርአት ተመሳሳይ ተግባር በመፈጸም ላት ይገኛል።

በወያኔ ዘረኛ አፈናና መድልዎ በሃገር ውስጥ ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ የመጣው ውጥረት ከ ቁጥጥር ውጪ ወጥቶ በቱንዚያና ለሌች የሰሜንና ሜካከለኛው ምስራቅ አገሮች እንደሆነው "የስልጣን ዘመኔን ያሳጥርብኛል" ብሎ እንቅልፍ ያጣው የመለስ ዘናዊ ቡድን የህዝቡን ትኩረት ወደ ጦርነት ለማዞር ባለፈው ሳምንት ኤርትራ ላይ ጦርነት ማወጁ በይፋ የተናገረ ሲሆን ምናልባትም የአሁኑ የወጣቶች ወታደራዊ ሃይል ምልመላ ከዚህ የጥፋት ተልእኮ ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንደማይቀር የውስጥ ምንጮች ገልጸዋል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## ወያኔ በንግድ የሚፎካከሩትን ድርጅቶች የማጥፋት ስልታዊ የጥቃት እርምጃውን ቀጥሎበታል። አዋሽ የግል ባንክ ተረኛ ነው

የአገሪቱን ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ በበላይነት በመቆጣጠር እስከልጅ ልጆቻቸው ኢትዮጵያን ለመግዛት አልሞ የተነሳው የትግራይ ገዢ ጉጇሌ ከህወሃት ጋር የጥቅም ሽርክና በሌላቸው የንግድ እና ኢኮኖሚ ተቋሞች ላይ ለአመታት እያካሄደ ያለውን ዘመቻ አሁንም እንዳላባራ ሰሞኑን በአዋሽ ባንክ ላይ የከፈተው የሃሰት ውንጀላ አጋለጠ።

ወያኔ ይህንን የጥቃት እርምጃውን በመቀጠል እና ተፎካካሪ የሆኑትን ድርጅቶች ለማዳከም በቅርቡ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማኅበርን ከ13 ዓመታት በላይ በፕሬዚዳንትነት የመሩትን አቶ ለይኩን ብርሃኑን ጨምሮ አሥር የሥራ ኃላፊዎች፣ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ 6,196,760.88 |ስድስት ሚሊዮን አንድመቶ ዘጠና ስድስት ሺ ሰባት መቶ ስልሳ ከሰማኒያ ስምንት| የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሪ ሰጥታቺሁአል በሚል ሰበብ በቅርቡ ክስ መስርቶባቸዋል።

የባንኩን ፕረዝደንት ጨምሮ በቁጥር አሥራ አንድ በሆኑት የአዋሽ ባንክ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ የተመሰረተው ይህ "ከውጭ ምንዛሪ አጠያየቅ፣ አፈቃቀድ፣ አጠቃቀምና ከግዢ ትዕዛዝ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ሕገወጥ ድርጊቶችን ፈጽማቺሁአል፣ በተጭበረበረ ሰነድ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የውጭ ምንዛሪ በመስጠቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰው ሠራሽ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዲያጋጥመው አድርጋቺሁአል፣ አዋጅና መመርያ እንዲጣስ አድርጋቺሁአል፣ በዋና ወንጀል አድራጊነትና ተካፋይ ሆናቺሁአል፣ በሌላ ሰው ጥቅምና የሥራ አመራር ላይ የተፈጸመ ጉዳት አድርሳቺሁአል በማለትና በሌሎችም ወንጀሎች ተጠያቂ ትሆናላቺሁ" የሚል እንደሆነ ሁኔታውን የተከታተለ ዘጋቢያችን ከላከው ዘገባ ለመረዳት ተችሎአል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የወያኔን ዕድሜ ሊያሳጥር ይችላል የሚል ውጥረት በአገሪቱ እየተባባሰ ነው

በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ አገሮች የተነሳው የጸረ አምባገነን ህዝባዊ እንቅስቃሴ በአገራችን ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ መነሳሳአት እየፈጠረ መሆኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ያሰባሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በላከልን ዜና ገልጸ።

ወያኔና ጥቂት የጥቅም ተጋሮቹ በሚቆጣጠሩት የአገሪቱ ሚዲያ የተለመደው የልማትና ዕድገት ፕሮፖጋንዳ መነዛቱ እንደቀጠለ ቢሆንም ህዝቡ ግን በዚህ የወያኔ ርካሽ ፕሮፖጋንዳ ሳይዘናጋ ጆሮውንና ልቡን በሊብያና በየመን እንዲሁም በሌሎች የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች እየተደረገ ባለው አብዮት ላይ እንደተከለ በዚህም ምክንያት ወያኔ በጭቆና ተቋማቱ አማካኝነት በህዝባችን ስነልቦና ውስጥ ተክሎት የቆየው የፍርሃት ዳመና እየተቀደደ መሆኑን ሪፖርተራችን ያሰባሰባቸው መረጃዎች ይፋ አድርገዋል። ወያኔ የአገዛዝ ዘመኑን ዕድሜ ለማራዘም አዲስ የከፈተው የ5 አመት ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ፕሮፖጋንዳ ቃሉ እራሱ በህብረተሰቡ ውስጥ ዘልቆ ሳይሰማ ሌላ የማታለያእና ማዘናጊያ ፕሮፖጋንዳ መሆኑ እንደታወቀበት በዚህም የተነሳ ባለፉት አስረተ አመታት ተገኝቶአል ተብሎ ጉራ የሚነዛበት ባለ ሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት በዕለታዊ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

# ድህነት እንዲያበቃ፤ የመለስ አገዛዝ ይብቃ!!!!

መለስን “በቃ!” ለማለት ከሚያስገድዱን ዋና ዋና ምክንያቶቻችን አንዱ እየተባባሰ የመጣው ድህነታችን ነው።

የመለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ለድህነታችን መባባስ ምክንያት መሆናቸው ዛሬ ለውጭ ተመልካች እንኳን ግልጽ እየሆነ ነው። መለስ አውቆና አቅዶ ድህነትን እያስፋፋ ነው። ድህነት ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ እየዋለው ያለው ዘርፈ ብዙ ውለታ ሲጤን ለወደፊቱም በመለስ አገዛዝ ድህነት እንደሚፋፋ እንጂ ትንሽም እንኳን እንደማይቀንስ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ድህነታችንን በብዙ መንገዶች መጠቀሚያው አድርጎታል። ድህነት ለመለስ ዜናዊ እያበረከታቸው ካሉት የውለታ ዓይነቶች አንዳዶቹን እንጠቃቅስ።

1. ድህነት በየወሩ በሚሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር የእርዳታ ገንዘብ በሥራ ኮንትራት ስም በመለስ ዜናዊና አዜብ መስፍን ዘመዶች ስም በውጭ አገራት ወደተከፈቱ የግል የባንክ ሂሳቦች እንዲገባ ማድረግ የቻለ አስተማማኝ የሃብት ምንጭ ነው። ድህነት ቀነሰ ማለት የመለስ፣ አዜብና ጓደኞቻቸው “ቢዝነስ” ከሰረ ማለት ነውና እነሱ በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ “ድህነት ቅነሳ” ወሬው እንጂ ተግባሩ ሊኖር አይችልም።
2. ድህነት የመለስ ዜናዊን ፋሽስታዊ አገዛዝ ሰብዓዊ ቅብ ሰጥቶታል፤ ዘወትር “ልማት” እና “ልማታዊ.” የሚሉ ቃላትን እንዲያነበንብና ለህዝብ አሳቢ መስሎ እንዲታይ እድል ፈጥሮለታል። መለስ ዜናዊ ድህነታችን በዋለለት ውለታ በመጠቀም ችጋርን እያባባሰ በአፉ ግን “በድህነት ቅነሳ ላይ ያተኮርኩ የልማት መንግሥት ነኝ” እያለ ለሃያ ዓመታት እንዲገዛን አስችሎታል።
3. ድህነት የመለስ ዜናዊ እና የአዜብ መስፍን ዘመዶች የኢትዮጵያዊያንን ደሳሳ ጎጆዎች እያፈረሱ በከተሞች ውስጥ ፎቆችን ስለገነቡ መልካም ነገር እንደሰሩ ተደርጎ እንዲታይላቸው ረድቷል። በየክልሉ ያሉ ምስለኔዎቻቸውም በዘረፉት ገንዘብ ህንፃ ሲገነቡ እና ፋብሪካ ሲያቆሙ “ልማታዊ ባለሃብት” ተብለው እንዲሞካሹ እድል ፈጥሮላቸዋል።
4. ድህነት የመለስ ዜናዊ ባልደረቦችና ምስለኔዎች የዛሬ ኑሮ ቀድሞ ይኖሩት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር የዛሬው የቱን ያህል የተሻለ እንደሆነ አስተውለው እንዲደሰቱ፤ ሰፊው ህዝብ ይበልጥ እየደኸየ በመሆኑ ደግሞ “ድላቸው” እንዳይነጠቅ ነቅተው እንዲጠብቁ አድርጎላቸዋል።
5. ድህነት ለአድርባዮች፣ ሆድ አደሮችና መስሎ አደሮች የሚወጣው ወጪ እጅግ አነስተኛ እንዲሆን አድርጎላቸዋል። ድህነት ለጥቂት ጉርሻዎች ክብራቸውን፣ ስብዕናቸውና ወገኖቻቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ደካሞች እንዲኖሩ አድርጓል።

መለስ ዜናዊ ግን በድህነት ላይ ተስፋውን የጣለው ከዚህም በላይ እንዲያደርግለት ነው። እንደ መለስ ምኞትማ በድህነት ምክንያት

- የመንግሥት ሠራተኛውን ለመኖር ሲል አለቆቹ “በል” ያሉት ብቻ እንዲል፤
- መሬቱ የተቀማ ገበሬ “ዘራፍ!” ማለቱን ትቶ እያለቀሰ ወደ ቀን ሥራው እንዲያዘግም፤
- ታክሲ ነጂውንና ነጋዴው አምርሮ እንዳይነሳ፤
- የዩኒቨርስቲ ተማሪን መፈክር መፃፊያና ቴሌፎን መደወያ እንኳን አጥቶ ተስፋ እንዲቆርጥ፤ እና
- ሌላም .... ሌላም እንዲሆን ይፈልጋል።

ሆኖም ለሁሉም ነገር ልክ አለው። ድህነትም የሚያደርገው ነገር ውስን ነው። ከዚህ በላይ ምን እንዳናጣ ነው የምንፈራው? ድህነት በእኛ ላይ እንደሰለጠነ አይቆይም። በጭራሽ!!! ድህነትን በመንፈስም፤ በገቢርም እንረታዋለን።

አሁን ግልጽ የሆነ ነገር አለ። ድህነትና መለስ ሸሪኮች ናቸው። መለስ ካልጠፋ ድህነት አይጠፋም።

ድህነትን ለማጥፋት በመጀመሪያ በአፍ “የልማት መንግሥታት ነን” ባዮች፤ በተግባር ግን የድህነት ሸሪኮች የሆኑ መንግሥታትን ማስወገድ እንደሚገባ ከቱኒዝያ፣ ግብጽ፣ ሊቢያ፣ የመን እና ሌሎችም የአካባቢው አገሮች ተጋድሎ ተምረናል።

“በድህነት ቅነሳ” ስም ድህነትን የሚያበዛ አገዛዝ ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ ተቀምጦ እያለ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ያልፍለታል ብሎ መጠበቅ የዋህነት መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ተረድተናል። የመለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚያበለጽገው እራሱን፣ ቤተሰቦቹን፣ ባልደረቦቹንና ባዕዳን “ኢንቬስተሮችን” መሆኑን በጣም ... እጅግ በጣም ... ግልጽ ሆኖልናል።

አገራችን ሃብታም፤ ህዝቧም ታታሪ መሆኑን እናውቃለን። በድህነት ላይ የቆረጠ መንግሥት ሳይኖረን ድህነትን ማስደንገጥ እንኳን አንችልም። ከድህነት የመውጫ መንገድ የሚጀመረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ማስወገድ መሆኑ ዛሬ የማያሻማ ሃቅ ሆኗል።

ድህነት በቃን!!! የድህነት ሸሪክ የሆነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቃን!!! ድህነትና መለስ ይወገዱ!!!!!

**በየቋንቋዎቻችን “በቃ!!!” እንበል!!!!**

**በቃ!!! ገዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

## በመለስ ዜናዊ የሚታዘዙ ፖሊሶች ለተቃውሞ ሰልፍ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

ወያኔ ያሰማራቸው ፖሊሶች ወደሰልፈኛው ምንም አይነት መሳሪያ እንዳልተኮሱ ነገር ግን በያዙት ቆመጥ ዱላ አቅም የፈቀደላቸውን ያህል የጭካኔ ድብደባ እንደፈጸሙ የገለጸው ዘጋቢያችን ክፉኛ ቆስለው የህክምና ዕርዳታ ለማግኘት ወደተለያየ ሆስፒታል የሄዱ ጉዳተኞች ምንም አይነት ዕርዳታ እንዳያገኙ እንደተከለከሉ አያይዞ ገልጾአል።

ፖሊስ በወሰደው በዚህ የሰላማዊ ሰልፍ ብተና እርምጃ ሰዎችን በትላልቅ የወታደር መኪና ሲያጓጉዝና ሲደበድብ ያየው የሰፈር ሰው ያለወትሮው ፖሊሶች ላይ ድንጋይ በመወርወርና በመሳደብ ታሳሪዎችን ለማስጣል የሞከረ ሲሆን በአንድ ጊዜ ወደ እስር ከተወሰዱ 80 ያህል ሰዎች 23ቱ ሲቀሩ ሌሎች ወዲያውኑ መለቀቃቸውን የዘጋቢያችን ሪፖርት አመልክቶአል።

በቱኒዚያ የተቀሰቀሰውና እስከ መካከለኛው ምስራቅ የዘለቀው ህዝባዊ አብዮት ያስደነገጣቸው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ ቆንጮዎች በአገራችን ተመሳሳይ ህዝባዊ ቁጣ ገንፍሎ ይወጣል በሚል ስጋት መንገዶችንና አደባባዮችን ሁሉ በፖሊስ እና ወታደር እንዳሳጠሩት ህዝብ ሊገናኝበት ይችላል ብለው የሚያስቡትን የመገናኛ ብዙሃንንም ለመዝጋት አሰፍስፈው እንዳሉ ምንጮቻችን ይናገራሉ።

## ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ወጣቶችን . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

በሰሜን አፍሪካዊቷ አገር በሊቢያ ላይ የጋዳፊ መንግሥት የከፈተውን ጭፍጨፋ ለማምከን የአለም አቀፍ ኮሚኒቲው እርምጃ መውሰዱ ”በአጋዚ ጦር ጥይት ሥልጣን ላይ ሊቆይ እችላለሁ” በማለት እራሱን ያጽናኛ የነበረውን የመለስና በረከት ቡድንን ክፉኛ እንዳስደነገጠ የሚናገሩ ምንጮቻችን ፤ ኤርትራን ለመውረር የሚደረገው ፉከራና ዛቻ ከተስፋ መቁረጥ የመነጨ ስሜት ከመሆን አልፎ የማንንም ኢትዮጵያዊ ብሄራዊ ስሜት ሊቀሰቅስ እንደማይችል ይልቁንም ወያኔ አያደርገውም እንጂ የስሌት ስህተት አድርጎ ጦርነቱን ቢጀምር የራሱን ግብአተ መሬት እንደሚያፋጥን በእርግጠኝነት ይናገራል።

## አባዱላ ገመዳ ወያኔን ጥሎ ለመኮብለል ሃሳብ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

የአባዱላ ገመዳን ባህሪ መለወጥ ያልወደደው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን በያዘው መከላከያ ሥልጣን ቢቆይ አደጋ ሊፈጥር ይችላል ከሚል ስጋት በዘዴ ከቦታው እንዳነሳውና ባለፈው ግንቦት 2002 በተካሄደው የወያኔ ምርጫ በኦሮሚያ ክልል የነበረውንም ሥልጣን ጭምር ተገፎ በአፈጉባኤነት ሥም በፈደራሉ ፓርላማ ውስጥ እንዲያገለግል እንደተመደበ ይታወቃል። ለመለስ ዜናዊ ቅርብ የሆኑ ምንጮቻችን በሰጡን መረጃ በኦህዴድና በህወሃት አመራር መካከል የኖረው የጌታና ሎሌ ግንኙነት ለያንዳንዱ የኦህዴድ አመራር ጥበቃ በሚመደቡ ተራ የህወሃት ጥበቃ አባላትና ደህንነት ሰዋች ሳይቀር እንዲናቁ ስላደረጋቸው አመራሩ ላለፉት 2 እና 3 አመታት በዚህ አሰራር እጅግ ሲከፉ ኖረዋል። መለስ ዜናዊና ባለቤቱ አዘብ መስፍን የተዘፈቁበትን ሙስናና የሃብት ዘረፋ እስከ ዛሬ ለአንዴም አንስቶ የማያውቀው የኢሃዴግ ግምገማ አባዱላን ጨምሮ በየደረጃው ያሉትን የኦህዴድ ሹማምንት በየጊዜው እያተራመሰ ከፊሉን ወደ እስር ቤት ከፊሉን ደግሞ ከሥራ በመፈናቀል ላይ እንደሚገኝ የግንቦት 7 ድምጽ በተደጋጋሚ ሲዘግብ ቆይቶአል።

ኦህዴድ በመለስ ዜናዊ የሚመራ የህወሃት አናሳ ቡድን ተለጣፊ በመሆን በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚፈጽመው ሰቆቃ ያንገፈገፈው የኦሮሞ ህዝብ በተለያየ አጋጣሚ ጥላቻውን ሲገልጽ እንደኖረ የሚታወቅ ሲሆን፤ በድህረ ምርጫ 97 ወያኔ የደረሰበትን ኪሳራ ለመሸፈን ዜጎችን በግዴታ አባል የማድረግ ዘመቻ ከከፈተ ወዲህ ለህወሃትና ተለጣፊው ኦህዴድ ጥላቻ ያላቸው በርካታ የኦሮሞ ተወላጆች በድርጅቱ ውስጥ በአባልነት በመግባት በወያኔ ላይ ችግር እየፈጠሩ እንዳለ ለማወቅ ተችሎአል። መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ኦህዴድንና ፈጣን ሎተሪን በማወዳደር “ሲፍቁዋቸው ሁሉም አነጎች ናቸው” በማለት ብሽቀቱን በአደባባይ እንደገለጸና እግረመንገዱን እንደበፊቱ ትዕዛዙን እልል እያሉ የሚያስፈጽሙ ሰዎች ቁጥር በድርጅቱ ውስጥ እያነሰ መመጣቱን አመላክቶአል።

ባለፈው መስከረም ወር አዳማ ላይ ተደርጎ በነበረው የኦህዴድ ስብሰባ አባዱላንና ከርሱ ጋር የሃሳብ አንድነት ያላቸውን ሰዎች በግምገማ ሥም ለማስመታት ህወሃት ጠንስሶት የነበረው ሴራ ባልተጠበቀ ሁኔታ በመክሸፉ መለስ ዜናዊ እጅግ ተበሳጭቶ እንደነበረ እና የእነ አባዱላን ወገን ገለል በማድረግ ታማኝ ናቸው ከሚላቸው አንዱ የሆነውን ሙክታር ከድርን የድርጅቱ ሰብሳቢና የክልሉ ፕሬዝዳንት አስደርጎ ለማስመረጥ የነበረው ዕቅድ ተደናቅፎ ከርሱ ፍቃድና ምኞት ውጪ ለመጀመሪያ ጊዜ የህወሃት ቁንጮዎች ምርቃት |Blessing/ ያላገኘ አለማየሁ አቶምሳ ስልጣን ለመያዝ በቅቶአል። በዚህም የተነሳ የመለስ ቡድን እስከዛሬ ደስተኛ እንዳልሆነና ኦህዴድን መፍራትና መጠራጠር እንደተጀመረ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከወያኔ መሪዎች በተለይም ከመለስ ዜናዊ እና ሳሞራ ዩኑስ ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ የገባው አባዱላ ገመዳ ጀርመን የሚገኘው እንደደረሰን ጥቆማ ለስደት ይሁን ወይም ለሌላ ጉዳይ ለማጣራት ተሞክሮ በቅርብ ለህክምና ወደታይላንድ ተጉዞ እንደነበረና ከዚያ በተመለሰ በጥቂት ቀናት ውስጥ በህክምና ሥም ወደ ጀርመን መምጣቱንና እስከ አለፈው ሰኞ መጋቢት 18 እዚያ እንደሚገኝ ከማረጋገጥ ውጪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት አልተቻለም። የግንቦት 7 ድምጽ የማጣራቱን ጥረት በመቀጠል ዝርዝር መረጃ እንደተገኘ ለአንባቢያን የሚያቀርብ መሆኑን ከወዲሁ ያስታውቃል።

# የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር በ1996 ዓ.ም ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ የቀረበ (በዶ/ር ታደሰ ብሩ)

## ጽሁፉ የያዛቸው በርካታ ቁም ነገሮች ስላሉ በዚህ ጋዚጣ በተከታታይ ለማቅረብ ችለናል (ክፍል 3 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ )

### 4.3. በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ /Consensually Unified National Elite/

በአንዳንድ አገሮች ያሉ ልሂቃን ከእርስ በርሳቸው መጠፋፋት ይልቅ ልዩነቶቻቸውን በማጥበብ መደራደርን፤ ሊደራደሩ ባልቻሉባቸው ጉዳዬች ደግሞ የሕዝብ ዳኝነትን ይመርጣሉ፡፡

በአንጃዎች መካከል ተመጣጣኝ ኃይል ሲኖርና አንዱ አንጃ ሌሎቹን ለማጥፋት የሞራል እና/ወይም የኃይል ብልጫ በሚያጣበት ጊዜ ልሂቃን ልዩነቶቻቸው ወደ ግጭት እንዳያመሩ መደራደርን ይመርጣሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቶቹ ድርድሮች በግለሰብ ደረጃ ተጀምረው በድርጅቶች ይቋጫሉ፡፡ ቀስ በቀስም ድርድር የሚደረግበት አጠቃላይ ደንብና ሥርዓት ወጥተው በሁሉም ወይም በአብዛኛዎቹ ልሂቃን ይከበራሉ፡፡ ለድርድር የማያመቹ ጉዳዮች (ለምሳሌ፤ መንበረ-ሥልጣን) የሚወሰኑበትን ሥርዓት ያበጃሉ (ለምሳሌ፤ ተራ መግባት ወይም ምርጫ)፡፡ ልሂቃኑ በድርድር መግባባት ያልቻሉበት ጉዳይ በሕዝብ ድምጽ እንዲወስን ሲስማሙ ፖለቲካ ድርድርም፣ ፉክክርም፣ ስለሚሆን የጠለቀ እዉቀት የሚጠይቅ የሙያ መስክ ይሆናል፡፡ በዚህ ዓይነት ማኅበረሰብ ፖለቲካ አሸናፊና ተሸናፊ ያለበት ቢሆንም እንኳን ካለመወዳደር ተወዳድሮ መሸነፍ የሚመረጥበት ጨዋታ ተደርጎ ስለሚወሰድ ማሸነፍ በጣም የሚፈለግ ቢሆንም መሸነፍ ግን የዚያን ያህል የሚመር አይሆንም፡፡ በሌላ አነጋገር ፖለቲካ ትርፍ ያለዉ ጨዋታ /positive sum game/ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ፖለቲከኛ ከእያንዳንዱ ድርድርና ክርክር የራሱን ወገን ጥቅም ለማብዛት ወይም የራሱን ወገን ጉዳት ለመቀነስ የሚጥር፤ ሃሳቡን በቀላል ቋንቋ ለአብዛኛው ሰው በሚገባው አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ የሚችል፤ አንደበተ ርቱዕ ጠበቃ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህም ምክንያት ፖለቲካ ታጋሽነትና ብልህነትን የሚጠይቅ ሕፃናት ሲያድጉ መሆን የሚመኙት የተከበረ ሙያ ነው፡፡ከእንዲህ ዓይነቱ ውድድርም በአሸናፊነት የሚወጡት አርቆ-አሳቢዎች፣ አስተዋዮች፣ ታጋሾቹና አንደበተ-ርቱኦቹ ልሂቃን ይሆናሉ፡፡ ለእንደዚህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ሰላም የድርደርና የመቻቻል ውጤት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ሰላምና ዲሞክራሲን ለማስፈን የተመቻቹ ሁኔታዎች ላይ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡ የተለያዩ ሃሳቦች በነፃነት የመንሸራሸራቸው ዕድልም የሰፋ በመሆኑ ለእድገት አመቺ ነው፡፡

በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያለው ማኅበረሰብ በሁለት ጽንፎች ማለትም በአንድ ጽንፍ እርስ-በርሳቸው የሚፃረሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ፣ በሌላኛው ጽንፍ ደግሞ በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ፣ መካከለ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የሁለቱንም ባህርያት በተለያየ መጠን የያዘ «ማክያቶ» ነዉ፡፡ ነጭ ማክያቶ፣ መካከለኛ ማክያቶ እና ጥቁር ማክያቶ እንዳለ ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ተፎካካሪዎች ጠላቶች መስለው የሚታዩና ድርድሮችም አስቸጋሪ ሲሆኑ (ለምሳሌ፤ ኢጣሊያ፣ ስፔን፣ እስራኤል፣...) ሌላ ቦታ ደግሞ በተፎካካሪዎቹ ልሂቃን መካከል ያለው ልዩነት ለይቶ ማውጣት እስከሚያቅት ደረስ ሊመሳሰሉብን ይችላሉ (ለምሳሌ፤ ዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ እንግሊዝ)፡፡

ለሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት በአንድነት መገኘት በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን መኖር አስፈላጊ ግን በቂ ያልሆነ ሁኔታ ነው፡፡ «በቂ ያልሆነ» የተባለው ዲሞክራሲ ቀደም ሲል የዘረዘርኳቸውና ሌሎችም ያልጠቀስኳቸው መዋቅራዊ ሁኔታዎችን ስለሚፈልግ ነው፡፡ እዚህ ላይ አጽንኦት ልሰጠበት የምፈልገው ጉዳይ ግን ጥሩ ሕገመንግስት፣ ጥሩ የምርጫ ህግ እና ግልፅና ፍትሃዊ ምርጫ ወ.ዘ.ተ. ቢኖሩም እንኳን ልሂቃኑ ለድርድር የተዘጋጁ ካልሆኑ ዲሞክራሲ መኖር የማይችል መሆኑ ነው፡፡

### በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ እንዴት መገንባት ይቻላል?

ለመደራደርና በሰላማዊ መንገድ ለመወዳደር ዝግጁ የሆኑ ልሂቃን ያሉበት ማህበረሰብን በእውቅ /deliberately/ መገንባት ይቻላልን? በራሱ የሚመጣስ ከሆነ እንዴት ነው የሚመጣው? ከየት ነው እንዲህ ዓይነቶቹ ልሂቃን የሚገኙት? ከሁሉም በላይ ደግሞ እርስ-በርሳቸው የሚፃረሩ ልሂቃን ካሉበት ማህበረሰቡ ተደራዳሪ ልሂቃን ወደአለበት ማኅበረሰብ እንዴት ነው መሸጋገር የሚቻለው? የሚሉት ጥያቄዎች መሠረታዊ ናቸው፡፡

ማንኛዉንም ማኅበረሰብ በእውቅ /deliberately/ መገንባት ስለመቻሉ በጣም አከራካሪ ቢሆንም አዉቀዉም ይሁን ሳያዉቁ ልሂቃን የሚያደርጉት ግን ይህንኑ ነዉ፡፡ አንዳንድ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ ሂግሌይ፣ ገንትኸር፣ በርተን፣ ቬሴሎቪች፣ ...) እንደሚሉት ተፃፃሪ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ በድርድርና ውድድር ወደሚለዝቡበት ማህበረሰብ ከሚከተሉት በአንደኛው መንገድ ሊሸጋገር ይችላል፡፡

### የውጭ ኃይል ተጽዕኖ

አንዲት አገር ጉልህ የውጭ ተፅዕና ካለባት የአገሪቱ ልሂቃን ቢያንስ በቁጥር የበዙቱ የውጭን ጠላት በጋራ ለመዋጋት ልዩነታቸውን ወደጎን በመተዉ የመቻቻል ዝንባሌ ያሳያሉ፡፡ ይህ በተለይ በቅኝ ግዛት ዘመን በጉልህ የታየ ክስተት ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መቻቻል አብዛኛዉን ጊዜ ከጋራ ድል በኋላ የሚፈርስ ቢሆንም አንዳንዴ ከድል በኋላም ቀጥሎ ለዘላቂ ድርድር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የአሜሪካ፣ የካናዳ፣ የኒውዘርላንድ፣ የአውስትራሊያ፣ የአየርላንድ፣ የሕንድ፣...፣ወዘተ ብሐራዊ ልሂቃንና እነሱን ተከትለው የመጡት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች በዚህ መንገድ የተገኙ ናቸው፡፡

### ቀስ-በቀስ መሃል ላይ የመሰባሰብ ዝንባሌ

ያለውን ሥርዓት አፍርሶ በሌላ የመለወጥ ዓላማ ያላቸው የግራም ሆነ የቀኝ አክራሪዎች ፈጣን ድል ካልተቀዳጁ በስተቀር ጽንፈኛ አቋማቸው እያደር የመሟሸሽ አዝማሚያ አለው፡፡ አክራሪነት ለአጭር ጊዜ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ማራኪ ሊሆን ቢችልም አንዱ አክራሪ ከሌላኛው ጽንፍ አክራሪ የማይšል መሆኑን ደጋፊዎች መገንዘባቸዉ ስለማይቀር እና ተደጋጋሚ ሽንፈት የሚያስከትለውም ኪሳራ ከፍተኛ በመሆኑ መሃል መንገድ ላይ ተገናኝተው ግራ-ቀመስ ወይም ቀኝ-ቀመስ መንግሥት በመመሥረት ጥያቄ ላይ መሟገትን ይመርጣሉ፡፡ በአንድ ወቅት አክራሪ የነበሩ የዴንማርክ፣ የኖርዌይ፣ የኢጣሊያን፣ የፈረንሳይ፣ የጃፓን ኮሚንስቶችና ፋሺስቶች አቋሞቻቸውን አለዝበው በሃገራቸው ፓርላማና መንግሥታት ቁልፍ ቦታዎችን በመያዝ አስተዳደሩን ወደእነሱ ለመሳብ መጣር ከጀመሩ ውሎ አድሯል፡፡ በዚህም አንዳንዶቹ ጥሩ ውጤት አስገኝተዋል፡፡

### ሰጥቶ መቀበል

ተደጋግሞ ሲፈፀም ባይታይም ከበለጠ ኪሳራ ለመዳን ሲሉ አንዳንዴ በሥልጣን ላይ ያሉ ልሂቃን ሥልጣናቸውን በድርድር ለተፋላሚዎቻቸው ሊለቁ ወይም ልዩነቶቻቸው እንዳሉ ሆነው በጋራ ለመስራት ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ በእንግሊዝ በ1688-1689፤ በስዊድን በ1809 በቡርዣዎችና በመሳፍንቱ መካከል ድርድር በመደረጉ በፈረንሳይ የፈነዳውን አይነት ሥር-ነቀል የቡርዣ አብዮት ሳያስፈልግ የሥርዓተ-ማኅበር ለውጥ ተደርጎል፡፡

በድርደሩ መሳፍንቱ ሥልጣናቸውን ለቀው ክብራቸውን አስጠብቀዋል፡፡ በአዲሱ ሥርዓትም አንዳንድ የቀድሞ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶችን የመጠበቅ ልዩ ስልጣን መሳፍንቱ በድርድሩ አግኝተዋል፡፡ በኮሎምቢያ 1957-1958 ሥልጣን ላይ የነበሩ ልሂቃን ቁልፍ ከሆኑ የመንግስት ሥልጣናት ግማሹን ለተቃዋሚዎች በመልቀቅ የፕሬዜዳንትነት ሥልጣንን በፈረቃ ሊለዋወጡ ተስማምተዋል፡፡

በቬንዙዌላ 1958 ሥልጣን ላይ የነበረው ልሁቅ ከተቃዋሚው ጋር ተደራድሮ ከፊል ሥልጣኑን በመልቀቁ ሊከተል ይችል የነበረውን ከፍተኛ የደም መፍሰስ በመቀነስ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት ጥሏል፡፡ በፖላንድ 1989 ሥልጣን ላይ የነበረው ኮሚኒስት ልሁቅ ከተቃዋሚው «ሶሊዳሪቲ» ልሂቃን ጋር በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተደራደሮ ፈርሞ ስልጣኑን ለቋል፡፡ በተለይ የፖላንድ የክብ ጠረጴዛ ዙርያ ድርድር አስደናቂ ክስተት ነበር፡፡ በ1989 የፖላንድ ኮሚኒስት ሥልጣኑን ላለመልቀቅ መግደርደር የሚያስችለው በቂ ኃይል ነበረው፡፡ ወታደራዊ ኃይል በፓርቲ አመራር ሥር ነበር፡፡ ሶሊዳሪት ግን የታጠቀ ሠራዊት አልነበረውም፡፡ ኮሚኒስቱ ወገን ወታደራዊ ኃይልን መጠቀም ባይፈልግ ወይም ባይችል እንኳን እንደ ሶቭየት ኅብረቱ ኮሚንስት ፓርቲ «ሽግግሩን የምመራው እኔ ነኝ» በሂደት ራሴም እየተለወጥኩ ነኝ ማለትና ዕድሜን ጥቂት ማርዘም ይችል ነበር፡፡ በዚህ ፈንታ በስምምነት ሥልጣኑን በመልቀቁ አገሩን ከአደጋ አድኗል፤ ክብሩንም አስጠብቋል፡፡
ዛሬ ይኸውም ልሂቅ አቋሙን ከልሶና አለዝቦ ሶšል ዴሞክራት ሆኖ በመቅረብ በዲሞክራሲያዊ ዉድድር በማሸነፍ በርካታ የስልጣን ወንበሮችን መልሶ ይዟል፡፡

በ1994 የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት መሪ ዲ. ክለርክና የነጻነት ተሚጋቹ ኔልሰን ማንዴላ እጅ ለእጅ ተጨባብጠው ወንበረ ሥልጣንን በመለዋወጥ የሰላምን የናቬል ሽልማት በጋራ አግኝተዋል፡፡ ዉዝግቡ በዚህ መንገድ በማለቁ የደቡብ አፍቃሪ ነጮች ከጥቁሮች ሊደርስባቸው ይችል የነበረውን የበቀል እርምጃ እንዳይኖር አድርጓል፡፡ የደቡብ አፍሪቃ ጥቁሮች ደግሞ ነጮችን ቢያባርሩ ኖሮ አገራቸው ሊደርስባት ይችል የነበረውን ኪሳራ እንዳይደርስ አድርገዋል፤ «ሰጥቶ መቀበል» ይሏል ይህ ነው፡፡

ከላይ እንደተብራራዉ «ገዥ መደብ በምንም ዓይነት ቢሆን ሥልጣኑን በፍቃዱ አይለቅም» የሚለውን አባባል አብዛኛዉን ጊዜ ትክክል ቢሆንም ሙሉ በሙሉና ሁሌ እዉነት አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በሥልጣን ላይ ያሉ ልሂቃን ተቃዋሚዎቻቸውን በጦር ኃይል ከማጥፋት ይህ ባይቻል ደግሞ በሚያሳዝን መልኩ በሶማሊያና ሩዋንዳ እንደታየዉ ከእርበርስ መጠፋፋት ይልቅ የይስሙላ የ«ሰላም ጥሪ» ሳይሆን ሥልጣናቸውን ከፍለው ወይም ሙሉ በሙሉ ለቀው ለተቃዋሚዎቻቸው የሚያስረክቡበት ሁኔታ መኖሩን ከላይ በተዘረዘሩት ምሳሌዎች ለመግለጽ ሞክሬያለሁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ክስተቶች በጣም አልፎ አልፎ ብቻ የሚያጋጥሙና ብርቅዬዎች ከመሆናቸዉም በላይ እያንዳንዱ ድርድር ከብዙ ዓለም-አቀፍና አገር-አቀፍ ሁኔታዎች እንዲሁም ከእያንዳንዱ አገር ባህል ጋር የተወሳሰቡ ናቸዉ፡፡ (ክፍል 4 ሳምንት ይቀጥላል)

## አየለ ጫምሶ የወያኔ መሣሪያ ሆኖ ቅንጅትን በማፍረሱ ካሳ እየወሰደ እንደሆነ ተጋለጠ

በምርጫ 97 ፉክክር ወቅት የወያኔን ተንኮልና ጸረ አገር ተግባር አፍረጥርጦ ያጋለጠው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ በአዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች በመለስ ዜናዊ ቋንቋ ወያኔን “በዝረራ በማሸነፉ” በትግራይ ገዢ ጉጂሌ ጥርስ ተነክሶበት እንዲፈርስ ሲዘመትበት የዘመቻው ተባባሪ ከነበሩ የቀድሞ ቅንጅት ተመራጮች አንዱ የሆነው አየለ ጫሚሶ የዝህብ ተስፋና አለኝታ የሆነውን ግዙፍ ፓርቲ ለማፍረስ ለተጫወተው ሚና ከፍተኛ የሆነ ካሳ እየተቀበለ መሆኑን ለግንቦት 7 የደረሰው መረጃ አጋለጠ።

በግንቦት 7 መረጃ ምንጮች መሰረት አየለ ጫሚሶ ወደ ቀጨነ መድሃኔአለም በሚወስደው መንገድ በአዲሱ ገቢያ ቀበሌ 01 ውስጥ ቀደም ስል አስረቶ የሚኖርበትን መኖሪያ ቤት የኢትዮጵያ መብራት ሃይል ግብር መሰብሰቢያ ብሮነት በወር በ30 000 ሰላሳ ሺ የኢትዮጵያ ብር እንዲከራየው ተደርጎ ለወያኔ ለሰራው ወለታ በህዝብ ገንዘብ አላግባብ የሆነ ጥቅም እያፈሰበት ይገኛል።

የአየለ መኖሪያ ቤት እንደማንኛውም ተራ ኢትዮጵያዊ ቤት በዘመናዊነት ተርታ የማይመደብ መሆኑ እየታወቀ ለወያኔ ለሰራው ጀግንነት ውለታ ለመክፈል ሲባል ይህንን ያህል የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፈለው መደረጉ አንድ ቀን ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል ያሉት የመረጃ ምንጮቻችን ቤቱ አሁን ባለው እጅግ ውድ ነው በተባለበት ሂሳብ እንኳ ቢሰላ በወር ከሁለት ወይም ከሶስት ሺ ብር በላይ ሊያወጣ እንደማይችል ማንም ሰው ያውቃል ብለዋል።

በዚህ አለአግባብ በሚከፈለው ክራይ እጅግ የተበሳጩ የአካባቢው ነዋሪዎች በተለያየ ጊዜ ለመብራት ሃይል ባለስልጣን ን ቤቱ ለቢሮነት ተስማሚነት እንደሌለው ውስጥ ለውስጥም የውሃ መተላለፊያው ቧንቧው ፈንድቶ ለጤና ተስማሚ ያልሆነ ሽታ እየፈጠረ ማስቸገሩን በመግለጽ አበቱታ እያሰሙ ቆይቶአል። ላልፉት አመታት የህዝብን አቤቱታ ጆቾ ዳባ ልበስ ሲል የኖረው መብራት ሃይል በ3 ወር ውስጥ ቢሮውን ወደሌላ ቦታ እንደሚያዛውር ህዝቡም እስከዚያው እንድታገስ ጠይቆአል። የመብራት ሃይል የአሁኑ ይሁንታ ምላሽ ወያኔ ይነሳብኛል ብሎ እየሰጋ ያለው ህዝባዊ ተቃውሞ የፈጠረው ፈቃደኝነት ነው ይህ ባይሆን እስከዛሬ የት ነበሩ እያለ ህዝቡ እየጠየቀ እንደሚገኝ የደርሰን መረጃ ያስረዳል።

## አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ፍንዳታ ደረሰ በፍንዳታው ሁለት ሰዎች በጽኑ መቁሰላቸው ታወቀ

በአዲስ አበባ ም እራባዊ ክፍል ልደታ አካባቢ በሚገኝ ፍርድ ቤት ጥግ ከፍተኛ ፍንዳታ መድረሱንና በፍንዳታውም ሁለት ሰዎች በጽኑ መቁሰላቸውን ሮይተርስ የዜና ወኪል ገለጸ:: ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ይህንን የሮይተርስ ዜና አስመልክቶ እስካሁን ምንም አይነት አፍሰላዊ መግለጫ ያልሰጠ ቢሆኑም እንደተለመደው ፍንዳታውን ያደረሱት ኢሃደግ እያስመዘገበ ያለው ልማት እና እድገት ለማጨናገፍ በኤርትራ የሚደገፉ ጸረ ሰላም ሃይሎች ናቸው ሊል እንደሚችል እየተጠበቀ ነው።

ፍንዳታውን አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡን ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነእዋሪ እስከ አሁን ሰለፍንዳታው ምንም የሰሙትና የሚያውቁት እንደሌለ ተናግረው በአሁኑ ሰአት የሚይዝና የሚጨብጠውን በማጣት እጅግ ተሸብሮ ያለው የመለስ አገዛዝ እንዲህ አይነት ሽብር እራሱ ፈጥሮ ሌሎችን ከመወንጀል እንደማይመለስ እንደሚያምኑ ተናግረዋል። አድማጮቻችን ይህንን ሮይተርስ ዘገበ ተብሎ ድህረ ገጽ ላይ ስላየነው ፍንዳታ በምንጮቻችን በኩል ለማጣራት ሞክረን እስከአሁን ያገኘነው መረጃ የለም። መረጃው እንደተገኘ ዝርዝሩን በሰፊው እንደምንዘግብ ከወዲሁ እናሳውቃለን።

## የኦሮሞ ነጻነት ግምባር ወታደሮች 22 የወያኔ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ማቁሰሉን ገልጹአል:: ከዚያም በሁአላ ማርች 19 ቀን በወሰደው ርምጃ የዘረኛው ወያኔ የመረጃ ሰራተኛ የሆነና በአካባቢው የሚኖሩ ዜጎችን በማዋከብ ይታወቅ የነበረ አጥፊ ወታደር አዲስ ከተማ ከተባለ ቦታ ላይ መግደሉን ጨምሮ ገልጹአል::

የኦሮሞ ነጻነት ግምባር በቅርብ ቀን ባወጣው መግለጫ ከአመታት በፊት ለሁለት ተከፍሎ የነበረው የግምባሩ ሃይል ወደ አንድ በመምጣት መዋሃዱን እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝብ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ በጋራ ክንዱን እንዲያነሳ ጥሪ ማቅረቡ ይታወሳል::

ዜጎች በወያኔ አገዛዝ ላይ ማመጻቸውን እንደቀጠሉ ነው።በምዕራብ ኢትዮጵያ በበደሌ ከተማ አንድ የቀድሞ ወታደር 2 የፖሊስ አባላትን ገድሎ ተሰወረ።

ወ|ር ነዚፍ አብደላ የተባለ የቀድሞ የአገር መከላኪያ ሠራዊት አባል መጋቢት 10 ቀን 2003 በቁጥጥር ሥር ሊያደርጉት የተላኩትን ሁለት የወይኔ ፖሊሶችን ገድሎ ሌሎች 2 ሰዎችን በማቁሰል እንደተሰወረ የግንቦት 7 ምንጮች ከሥፍራው ገለጹ።

እንደምንጮቻችን ዘገባ ወታደር ነዝፍ ቀደም ሲል ይኖርበት ከነበረበት የገጠር መንደር ወደ በደሌ ከተማ ተዛውሮ እራሱንና ቤተሰቦቹን ለማስተዳደር የተገኘውን ሥራ ሁሉ በመሥራት ላይ የነበረ ሲሆን፤ አካባቢውን የሚያስተዳድሩት የወያኔ ሹሞች አመጽ ሊቀሰቀስ ይችላል በሚል ስጋት በተቃዋሚነት የሚጠረጥሩዋቸውን የኦሮሞ ተወላጆች ማሰር በመጀመራቸው የጥቃት ኢላማ ለመሆን የበቃ ሰው ነው። ወታደር ነዚፍን ለመያዝ ወደመኖሪያ ቤቱ የተላኩት ፖሊሶች ከተጠርጣሪያቸው መኖሪያ ቤት እንደደረሱ በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ለምርመራ እንደሚፈለግና በአስቸኳይ ከነርሱ ጋር እንዲሄድ አዘውት እንደነበር የገለጹት ምንጮች፤ ምንም ወንጀል ወይም ህገ ወጥ ድርጊት ያልፈጸመ ሰላማዊ ሰው ለምን ፖሊስ እንደሚፈልገው ግልጽ እንዳልሆነለት ሲያንገራግር ከቆየ ቦኋላ ትዕዛዛቸውን ከመፈጸም ሌላ አማራጭ እንደሌለው የተረዳው ነዚፍ በተሰጠው የሃይል ማስጠንቀቂያ እሺታውን ገልጾ ጥቂት ርቀት ከመሃላቸው ሆኖ ከተጓዘ ቦኋላ በድንገት የአንደኛውን ጠመንጃ በመቀማት መሳሪያ ያልያዘውን ሌላኛውን የፖሊስ ባልደረባ ተኩሶ እንደመታ ከዚያም ወዲያው ፊቱን መሳሪያውን ወደተቀማው ፖሊሲ በማዞር እሱንም እንደደገመው እና በጊዜው ከፖሊሶቹ ጋር የነበሩትን እና ሊይዙት የሞከሩትን ሌሎች ሁለት ሰዎች በማቁሰል ለማምለጥ እንደቻለ ይገልጻሉ።

የቀድሞ ጦር ሲበተን ድንበር አቋርጠው ወደሱዳን ከተሰደዱትና የሱዳን መንግሥት አሳልፎ ለወያኔ ከሰጣቸው ወታደሮች አንዱ የነበረው ወ|ር ነዚፍ ከበደሌ ከተማ ወጣ ብላ በምትገኘው ገጠር ሲኖርም ሆነ ወደ ከተማ ከዞረ ቦኋላ በመልካም ስነምግባሩ የሚታወቅ ዜጋ እንደሆነ በቅርበት የሚያውቁት ይናገራሉ። ሆኖም የወረዳው ባለሥልጣናት ሰውየው ካመለጠ ቦኋላ “ሊበቀለን ይችላል” ከሚል ፍርሃት ህብረተሰቡ ውስጥ እንዳይደበቅ “የአልካይዳ ምልምል ሆኖ በመገኘቱ” ሊታሰር ሲል ህግ አስከባሪዎቹን ገድሎ እንደተሰወረ በከተማው ውስጥ በሰፊው እያሰወሩ መሆኑን ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

አገዛዙ በኦሮሚያ ክልል ይቃወሙኛል ብሎ የሚፈራቸውን ሁሉ የኦነግ ደጋፊዎች ናቸው በሚል ሲያዋክብ፤ ሲያስርና ከሥራ ሲያፈናቅል እንደነበረ የሚያስታውሱ የበደሌ ነዋሪዎች ያ የወያኔ አሰራር አፍቃሪ ኦነግን እያበዛ በመምጣቱ በተለይ የሙስሊም እምነት ተከታይ የሆኑትን የኦሮሞ ተወላጆች በኢስላም አክራሪነት እና በአልካይዳ ምልምልነት መወንጀል እነደጀመረ ይናገራሉ። በበደሌ ከተማ ለዘመናት የኖሩትን የሌላ ብሄረሰብ አባላት ከኦሮሞ ጋር ለማጋጨት ለአመታት የተሰራው ሴራ ምንም ውጤት ባለማስገኘቱ የተከፋው የወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃይማኖት ሽፋን በክርስቲያኑንና ሙስሊሙ መካከል አለመተማመንን በመፍጠር ላይ እንደሚገኝ ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል።

በሃያ አመቱ የከፋፍለህ ግዛ ዘረኛ የወያኔ ፖሊሲ የተማረሩት ኢትዮጵያዊያን በደቡብ፤ በአማራና በአፋር ክልሎች በወያኔ ፖሊሶችና ጸጥታ ሰራተኞች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ እየወሰዱ ማምለጣቸውን ኢሳት የተባለው የኢትዮጵያ ሳተላይት ተሌቪዢን ደጋግሞ ገልጾአል።

## የወያኔን ዕድሜ ሊያሳጥር ይችላል የሚል ውጥረት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኑሮ ውስጥ ሳይታይ ይልቁንም የሰው ኑሮ መቋቋም አቅም እየተዳከመ በመጣበት በ5 አመት እድሜ በአለም ካሉት ባለመካከለኛ ገቢ ኑሮ ደረጃ እናደርሰሃለን ማለት በሚሊዮኖች ስቃይና መከራ ባለጊዜዎች የሚቀልዱበት እንደሆነ በሰፊው ግንዛቤ ተጨብጦበታል ተብሎአል።

ሰሞኑን አርባ ምንጭ ድረስ ተጉዞ የነበረው ዘጋቢያችን እንደገለጸው ላለፉት 3 ወራት በከተማው ውስጥ የንጹህ ወሃ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ ተቋርጦአል ሊባል ከሚችልበት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለረጅም ጊዜ በከተማው የነበረው የመብራት ችግርም እየተባባሰ እንደመጣ በዚህም የተነሳ ህዝብ መንግሥት አለን ብሎ ለማመን ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶአል። በከተማው ውስጥ ያነጋገራቸው ወጣቶች፤ ጎልማሶችና ሽማግሌዎች በሙሉ እንደግብጽ እና ቱንዚያ ህዝብ ሆ ብሎ በመነሳት ወያኔን ከትከሻችን ላይ ማውረድ ብቻ መፍትሄ ሊሆን እንደሚችል ይስማማሉ። በአዋሳ ፤ በጎባ፤ በይርጋለም፤ በሻሸመነ ፤ በሆሳና ና ሌሎች የደቡብ ከተሞች ያለው የህዝብ ብሶትና ቁጭት ሁሉ ከአርባምንጭ ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው የተሰባሰበው መረጃ ያመለክታል።

ይህ በዚህ እንዳለ “ምንም አይነት ህዝባዊ አመጽ ይነሳል ብዬ እንቅልፍ አጥቼ አላድርም ያለው” ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን እንደለመደው ቪ ኦ ኤ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮን ማፈኑን ፒተር ሃይንላይነ የተባለው የቮ ኦ ኤ ጋዜጠና ከአዲስ አበባ ማስተላለፉን ረዲዮ ጣቢያው ዘግቦአል። ወያኔ ህዝባው ተቃውሞ ሊነሳብኝ ይችላል ብሎ በሚሰጋባቸው ጊዜያቶች ሁሉ ህዝብ ነጻ የሆነ መረጃ እንዳያገኝ ከውጪ ወደ አገር የሚተላለፉትን ስርጭቶች በሞገድ ጠለፋ እንደሚያስተጓጉል ይታወቃል።

በተለያዩ አቅጣጫዎች ሊፈነዳ የተቃረበው ህዝባዊ አመጽ እንቅልፍ የነሳቸው የትግራዩ ገዢ ጉጂሌ የሬዲዮና ቴለቪዥን አፈና እርምጃ ከመውሰዱ በተጨማሪ ንጹሃን ዜጎችን በገፍ ማሰር መቀጠላቸው ቀደም ብሎ መዘገቡ ይታወሳል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ከተሞች አመጽ ለማስነሳት ከሽብርተኞች ጋር አሲራችኋል በሚል በርካታ የኦሮሞ ተወላጆች በየእስር ቤቱ እየተጣሉ መሆኑንና በተለይ በሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚታወቁ የአፍዴንና የኦብኮ አባላት በእንግልት ላይ መሆናቸው መገለጹ ይታወሳል።

የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ አምባገነኑ መለስ ቀደም ብሎ በነበረ ቃለ ምልልስ ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳ የሚችልበት ምንም ምክንያት የለም፣ ህዝብ ስልጣን ካስረከበን ገና አስር ወራት ሆኖት እያለ ከስልጣን እንድንወርድ የሚፈልግበት ምንም ምክንያት የለም በማለትና ውስጣዊ ጭንቀቱን ለማደባበስ በመሞከር አስገራሚ ንግግር ማድረጉ ይታወሳል::

## ወያኔ በንግድ የሚፎካከሩትን ድርጅቶች የማጥፋት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህንን አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡን ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ የባንኩ ከፍተኛ አመራር፣ እንዲህ አይነቱ ከፖለቲካ እና የወያኔ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በሃሰት እየተፈበረኩ በዘጎች ላይ የሚከፈቱ ክሶች የመጀመሪያ እንዳልሆን ገልጸው የአሁኑን ክስ ከሌሎች የፖለቲካ ክስ የሚለየው በአገሪቱ ውስጥ ያለው የኑሮ ውድነት፤ ሥራ አጥነትን እና ድህነት አድጎአል የሚባለው የ ኢኮኖሚ ዕድገት ጋር መጣጣሚ ተስኖት ዜጎች ብሶታቸውን በአደባባይ መግለጽ በጀመሩበት ምናልባትም ከሰሜን አፍሪካው አብዮት ልምድ ቀስመው ችግራቸውን ለመፍታት ወኔና ብርታት ባገኙበት መሆኑ ነው ስለዚህም ወደ እስር ቤት ብንላክም እንደቀደምቶቹ የፖለቲካ እስረኞች እዚያው ሳንበሰብስ ልንወጣ እንደምንችል ተስፋ የሰንግንበት ሰዓት ላይ የመጣ ውንጀላ ነው ብለዋል።

በመጨረሻም በደርግ ዘመን በግልጽ ይታይ እንደነበረው ሁሉ ወያኔዎችም ህዝብን በማስፈራራትና በገፍ ወደ እስር ቤት በማጎር ስልጣን ላይ ተቆናጥጦ መቆየት የሚቻል መስሉአቸው ከሆነ ይህ ስልት ያለቀበትና ያለፈበት መሆኑን አውቀው ከዚህ ተግባራቸው ቢታቀቡ ምናልባት አወዳደቃቸውን የተሻለ ሊያደርግላቸው ይችላል በማለት አስተያየታቸውን አጠናቀዋል::

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org